የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር

# አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ

# ADDIS NEGARI GAZETA

OF THE CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

አራተኛ ዓመት ቁጥር ፵፰
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፮ ቀን ፲፱፻፺፰ ዓ.ም.

በአዲስ አበባ ከተማ ባለአደራ ጊዜያዊ አስተዳድር ጠባቂነት የወጣ

4th Year No. 48
ADDIS ABABA 4th May., 2006

ማውጫ

CONTENTS

ደንብ ቁጥር ፳፩/፲፱፻፺፰

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ደንብ.....................................ገጽ ፯፻፲፫

REGULATIONS NO. 21/ 2006

THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT ENVIRONMENTAL IMPACT ASSESSMENT REGULATIONS............................................Page 713

## ደንብ ቁጥር ፳፩/፲፱፻፺፰
## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ደንብ

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የልማት ሀሳብ ንድፍ ሲዘጋጅ በታው ሲመረጥ ሲገነባ ወይም ሲተገበር እንደዚሁም በመተግበር ላይ ያለ እንቅስቃሴ ሲሻሻል ወይም ሲቋረጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በመተንበይና አስቀድሞ በማረም በቅጡ የታሰበበትን ልማት ለማምጣት የሚያግዝ በመሆኑ፣

በማህበራዊና በተፈጥሮአዊ አካባቢ ላይ ጉልህ አሉታዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ያደርሳሉ ተብለው ለሚገመቱ የማህበራዊና የልማት ፕሮጀክቶች ሥራው ከመጀመሩ በፊት በማህበረሰባዊና በተፈጥሮአዊ አካባቢ ላይ የሚያስከትለውን አሉታዊ የአካባቢ ተፅዕኖ ለመቀነስና ለማገድ በቅድሚያ መርምሮ ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

በአስተዳደሩ ውስጥ የሚካሄዱት የልማት እንቅስቃሴዎች የአካባቢን ደህንነት ሳያናጉና ከዘላቂ የልማት መርህ ጋር በተስማማ ሁኔታ ተፈፃሚ መሆናቸውን መከታተልና ማረጋገጥ አስፈላጊ በመሆኑ፣

## *REGULATIONS NO. 21/ 2006*
## *THE ADDIS ABABA CITY GOVERNMENT ENVIRONMENTAL IMPACT ASSESSMENT REGULATIONS*

WHEREAS, environmental impact assessment is used to predict and mange the environmental effects which a proposed development activity as a result of its design sitting, construction, operation, or an ongoing one as a result of its modification or termination, entails and thus helps to bring about intended development;

WHEREAS, it is found necessary to ascertain in advance the examination of those social and natural environment of negative significant impact to be presumed social and development projects in order to reduce and suspend the following negative environmental impact on the community and natural environment before the commencement of the work;

WHEREAS, it has become necessary to follow up and ascertain those undertaking development activities in the City to be implemented inconformity with the conditions of the principle of sustainable development and without obstructing environmental security;

ያንዱ ዋጋ
Unit Price 8.70

አዲስ ነጋሪ ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ
Addis Negari Gazeta P.O.Box 2445

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አስተዳደራዊ ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ በአጠቃላይ ራሱንና አካባቢውን በሚመለከቱ የልማት ዕቅዶች አወጣጥና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሕዝቡን በተለይ ለማሳተፍ የሚረዳ ህግ ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፣

የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ አስተዳደር በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 አንቀጽ 66(2) እና በአዲስ አበባ ከተማ መሪ ፕላን አዘገጃጀት፣ አወጣጥና አፈፃፀም አዋጅ ቁጥር 17/1996 አንቀፅ 29(2) ሠ መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

**፩. አጭር ርዕስ**

ይህ ደንብ «የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ» ደንብ ቁጥር ፳፩/፲፱፻፺፰ ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. ትርጓሜ**

በዚህ ደንብ ውስጥ፦

፩. «አካባቢ» ማለት በመሬት፣ በአካባቢ አየር፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በህያዋን፣ በድምፅ፣ በሽታ፣ በጣዕም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነ ውበት ሳይወሰን በተፈጥሮአዊ ሁኔታዎች ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ እንዲሁም መጠናቸው ወይም ሁኔታቸው ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ መስተጋብሮቻቸው ድምር ነው።

፪. «ተፅዕኖ » ማለት በአካባቢ ወይም በንዑሳን ክፍሎች ላይ በሚፈጠር ለውጥ ምክንያት ማንኛውም በአካባቢያዊ፣ በማህበራዊና በኢኮኖሚያዊ ወይም በባህላዊ ገጽታዎች ላይ የሚከሰት ተከታይ ለውጥ ነው።

፫. «የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ» ማለት አንድ ፕሮጀክት የሚያስከትለውን ገንቢም ሆነ አፍራሽ ውጤት በቅድሚያ ለይቶ የማወቂያና የመመዘኛ ዘዴ ነው።

፬. «የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ሰነድ» ማለት በፕሮጀክት ባለቤቶች ለማህበረሰባዊና ለአካባቢያዊ ደህንነት ሲባል የሚወሰዱ እርምጃዎችን አስመልክቶ ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ የጥናት ሰነድ ነው።

፭. «ፕሮጀክት» ማለት በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ ማንኛውም መመሪያ ውስጥ በተጠቀሰው ርዕስ የሚካተት ማንኛውም አዲስ የልማት እንቅስቃሴ ወይም በነባር ድርጅት ላይ የሚደረግ ጉልህ መስፋፋት ወይም ለውጥ ወይም ደግሞ ተቋርጦ የነበረ ሥራን መልሶ ለመጀመር የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው።

፮.«የፕሮጀክት ባለቤት» ማለት ፕሮጀክቱ በመንግስት የተወጠነ ሲሆን የሚመለከተው የመንግሥት አካል፣ ወይም በግሉ ዘርፍ የተወጠነ ሲሆን ባለሀብት የሆነው ሰው ነው።



WHEREAS, it has become necessary to enact law that environmental impact assessment serves to bring about administrative transparency and accountability as well as in particular that helps the public participate in the planning of and decision taking on development may affect them and its environment;

NOW, THERE FORE, the provisional Government of Addis Ababa City pursuant to Article 66(2) of the Addis Ababa City Government Revised Charter Proclamation No. 361/2003 and Article 29 (2) (e) of the Addis Ababa City Master plan Preparation, Issuance and Implementation Proclamation No. 17/2004 hereby issued these Regulations as follows:

## PART ONE
## General Provisions

***1. Short Title***

These Regulations may be cited as the "Addis Ababa City Government Environmental Impact Assessment Regulations No. 21/2006."

***2. Definitions***

In these Regulations:

1. "Environment" means the totality of all materials weather in their natural state or modified or changed by human; their external spaces and the interactions which affect their quality or quantity and the welfare of human or other living beings, including built not restricted to land atmosphere, weather and climate, water, living things, sound, odor, taste, social factors, and aesthetics;
2. "Impact" means any change to the environment or to its component that may affect environmental, social, economical and cultural features;
3. " Environmental Impact Assessment" means the methodology of identifying and evaluating in advance any effect be it positive or negative, which results from the implementation of a proposed project;
4. "Environmental Impact Study Instrument" means a study instrument submitted to the Authority concerning to measures to be taken for communities and environmental security;
5. " Project" means any new development activity under any category listed in any directive issued pursuant to these regulations, major expansion or alteration or any existing undertaking, or resumption of work that has been discontinued;
6. "Proponent" means any organ of government if in the public sector or any person if in the private sector that initiates a project;

፯. «ማስፋፋት፣ መለወጥ፣ ወይም ማሻሻል» ማለት የነባር ድርጅትን የሙሉ አቅም ምርት ወይም አገልግሎት ወይም ተግባራዊ ያልሆነ ጥናትን ከሀያ አምስት በመቶ በላይ በእሴት ማሳደግ ሲሆን፣ ይህም በዓይነት ወይም በመጠን ወይም በሁለቱም መጨመርን የሚያጠቃልል ነው፡፡
፰. «የመንግስት ሰነድ» ማለት ፖሊሲ፣ ስልት፣ መርሐ ግብር ሕግ ወይም የዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፡፡
፱. «አስተዳደር» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ነው፡፡
፲. «ፈ ቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት » ማለት እንደሁኔታው የኢንቨስትመንት፣ የንግድ ወይም የሌላ የሥራ ፈቃድ ለመስጠት በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ማናቸውም የመንግስት አካል ነው፡፡
፲፩. «ባለሥልጣኑ» ማለት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ነው፡፡
፲፪. «ድርጅት» ማለት በንግድ ሕጉ መሠረት ወይም በሌሎች ሕጎች የተቋቋመና በንግድ ሥራ ላይ የተሠማራ የማምረቻ ወይም የማከፋፈያ ወይም የአገልግሎት መስጫ ተቋም ነው፡፡
፲፫. «ሰው» ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ ደንብ መንግሥታዊ/ መንግሥታዊ ባልሆኑና በግል ባለሀብት በሚቀርቡ የልማት ፕሮጀክቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፡፡

፬. <u>የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ስለሚያስፈልጋቸው ፕሮ ጀክቶች</u>

፩. በዚህ ደንብ መሠረት የሚወጣ መመሪያ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውና የማያስፈልጋቸውን የፕሮጀክት አይነቶች ለይቶ ማሳየት አለበት፡፡
፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) የተጠቀሰው መመሪያ፡-
ሀ. አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው ስለማይታሰቡ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የማያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች፣ እና
ለ. አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው ስለሚታሰቡ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች፣ እና የመንግስት ሰነዶችን፣ ለይቶ ማመልከት አለበት፣

<u>ክፍል ሁለት</u>

<u>የግምገማ ሂደትን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች</u>

፭. <u>ጠቅላላ ድንጋጌዎች</u>

፩. በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ መመሪያ በአካባቢ ተፅዕኖ በግምገማ ሥር ማለፍ ያለባቸው ፕሮጀክቶች ከባለሥልጣኑ የብቃት ማረጋገጫ ሳያገኙ ሥራ አይጀምሩም፡፡

7. "Expansion, alteration or modification" means the upgrading of an asset more than 25 percent of an existing organization or service or non-implemented study; this shall include in kind or in amount or added in both;
8. "Public Instrument" means a policy, a strategy, a programme, a law or an international agreement;
9. " Government" means the Addis Ababa City Government;
10. "Licensing Agency" means any organ of government empowered by law to issue an investment permit or a trade or operating license or other work permit as the case may be;
11. "Authority" means the Addis Ababa City Government Environmental Protection Authority;
12. "Organization" means an institution established in accordance with commercial law or by other laws and engaged in a production or distribution or a service delivery business activity;
13. "Person" means a natural or juridical person.

*3. Scope of Application*

These Regulations shall be applicable on development projects proposed by Government or non- Government and private investors.

*4. Projects Requiring Environmental Impact Assessment*

1. A directive issued Pursuant to these regulations shall indicate separately those types of projects that do or do not require environmental impact assessment.
2. A directive provided under sub-Article 1 of this Article shall, among other things, determine categories of
   (a) Projects not likely to have negative impacts, and so do not require environmental impact assessment;
   (b) Projects likely to have negative impacts and thus require environmental impact assessment and public instrument;

*PART TWO*

*Provisions Concerning Impact assessment Process*

*5. General Provisions*

1. Those Projects that under go environmental impact assessment in accordance with a directive issued under these regulations shall not commence work without acquiring certificate of competence from the Authority.

፪. ማናቸውም ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት የኢንቨስትመንት፣ የንግድ ወይም የሌላ የሥራ ፈቃድ ከመስጠቱ በፊት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን ከባለሥልጣኑ ይሁንታ መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት::
፫. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት በተለያዩ ዕርከኖች የሚካሄድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስከትለው ወጪ በፕሮጀክቱ ባለቤት ይሸፈናል::
፬. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት በባለሥልጣኑ የተሰጠ የብቃት ማረጋገጫ የፕሮጀክቱን ባለቤት ከተጠያቂነትና ከኃላፊነት ነፃ አያደርገውም::

፮. <u>የተፅዕኖ መወሰኛ ታሳቢዎች</u>

፩. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ በባለሥልጣኑ የሚዘጋጁ መሥፈርቶችን እና ሌሎች አግባብነት ያላቸውን የአሰራር መመሪያዎች ወይም የአካባቢ ደረጃዎች መሰረት በማድረግ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚባሉትን ባለሥልጣኑ ሊወስን ይችላል::
፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) የተደነገገው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፕሮጀክቶች ጉልህ ተፅዕኖ፡-
   ሀ. ለጉዳት ከሚጋለጠው የሕዝብ ብዛት፣
   ለ. ለጉዳት ከሚጋለጥ ክፍለ አካባቢዎች፣
   ሐ. የሚከተለው ተፅዕኖ ከሚቆይበት ጊዜ፣
   መ. በአጭርና በረዥም ጊዜ በስፍራው የሚገኙ የልማት እንቅስቃሴዎች የታቀዱትን ጭምር የሚያስከትሉትን ድምር ጫና፣
   ሠ. የሚከተለውን ተፅዕኖ ለመቋቋም የሚቻል ወይም የማይቻል መሆኑን፣
   ረ. የልማት እንቅስቃሴውን ተከትለው ከሚፈጠሩ ተፅዕኖዎች እና ከሌሎች ተፈላጊ ሁኔታዎች አኳያ ይወሰናል::
፫. ፕሮጀክቱ ጎጅና ጠቃሚ ገፅታ ኖሮት ጉዳትና ጥቅሙ ተቀራራቢ ሲሆን ወይም ጉልሕ አሉታዊ ተፅዕኖ የመከተሉ ሁኔታ አሻሚ ሲሆን ፕሮጀክቱ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ ያደርሳል ተብሎ መገመት አለበት::
፬. በዚህ ደንብ መሠረት በሚወጣ መመሪያ በተዘረዘሩት ፕሮጀክቶች ላይ ብቻ ሳይወሰን ባለሥልጣኑ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትሉ ፕሮጀክቶችን ዓይነትና ባህሪ መለየት፣ መመደብ፣ ማሻሻል ወይም መለወጥ ይችላል::

፯. <u>የተፅዕኖ ግምገማ ሂደት</u>

በዚህ ደንብ መሰረት የሚካሄድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደት፡-
፩. ቀዳሚ ምርመራና ማጣሪያ ማድረግን፣
፪. የጥናት ትኩረት መወሰን፣
፫. የተፅዕኖ ጥናት ማካሄድ እና የጥናት ሰነድ ማዘጋጀትን
፬. የጥናት ሰነድ ምርመራን፣እና
፭. የክትትልና ቁጥጥር መርሀ ግብር ዝግጅትን፣
ያጠቃልላል::

፰. <u>ቀዳሚ ምርመራና ማጣሪያ</u>

፩. የፕሮጀክት ባለቤት ፕሮጀክቱ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ አያስከትልም ብሎ ሲያምን እና በዚህ ደንብ አንቀፅ (9) ድንጋጌ መሠረት ሙሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሂደትን ከማለፍ ነጻ እንዲደረግ ሲፈልግ ይሄንኑ ሁኔታ አስመልክቶ ያዘጋጀውን ቀዳሚ የፕሮጀክት መግለጫ ሰነድ ከማመልከቻ ጋር ለባለስልጣኑ ማቅረብ ይችላል::

2. Any licensing agency shall, prior to issuing an investment Permit or a trade or other operating license for the project, ensure that the Authority has authorized its implementation.
3. Cost entailed due to the undertaking of environmental impact assessment in different levels pursuant to the provisions of these regulations shall be covered by the proponent.
4. A certificate of competence issued by the Authority pursuant to these regulations does not exonerate the proponent from liability and responsibility.

*6. Considerations to Determine Impact*

1. Without Prejudice to Sub-Article (2) of this Article, the Authority may determine on a significant impact based on the criteria prepared by the Authority and others appropriate work procedures or environmental standards.
2. Without Prejudice to the generality of the Provisions of Sub-Article(1) of this Article, a significant impact of the Projects shall determine:
   (a) The number of population exposed to damage;
   (b) the sub- environments exposed to damage;
   (c) the duration of the impact followed there of;
   (d) in the short and long term development activities found in the area including the planed ones that the total impact to be followed;
   (e) Weather the possible impact to be resisted or not;
   (f) Impacts produced following the development activity and inconsideration of other necessary conditions.
3. Where the project has harmful and useful feature while a balance is shown between the harm and the use, or where there is a likely hood of a negative significant impact, the project shall be presumed to cause negative significant impact.
4. Without limiting on project specified in accordance with a directive issued pursuant to these regulations, the Authority may separate assign, modify or alter the kind and characteristics, of those projects, which cause negative significant impact.

*7. The process of Impact Assessment*

The process of impact assessment to be undertaken in accordance with these regulations shall include:
1. Making censorship and refinement;
2. Determine the study focus;
3. Undertake impact study and prepare study document;
4. Examining study document; and
5. Follow up and supervision of action plan preparation.

*8. Censorship and Refinement*

1. When the proponent believed that the project shall not cause negative significant impact and he seeks the whole environmental impact assessment require to be undertaken free from the process in accordance with Article (9) of these regulations, the proponent may submit the prepared document that describe the project with application.

፪. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ(1) መሠረት የፕሮጀክት መግለጫ ሰነድ እና ማመልከቻ ባለስልጣኑ በመቀበል በአመልካቹ ፕሮጀክት ላይ የማጣሪያ ምርመራ ያካሂዳል።

፫. በፕሮጀክቶች ላይ ቀዳሚ ምርመራ ለማካሄድ ማናቸውንም መረጃዎች ባለሥልጣኑ መጠቀም ይችላል። ሆኖም የቀረበለት መረጃ ውሳኔ ለመስጠት በቂ ሆኖ ካላገኘው ተፈላጊው ጥናት እንዲካሄድና መረጃዎቹም ተሟልተው እንዲቀርቡለት ማድረግ አለበት።

፱. <u>የማጣሪያ ውሳኔ</u>

ቀዳሚ ምርመራ እና የማጣሪያ ሥራው ካበቃ በኋላ ባለስልጣኑ

፩. ፕሮጀክቱ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ የማያስከትል ሆኖ ሲያገኘው ተግባራዊ እንዲሆን መስማማቱን የሚገልጽ ማስረጃ ለአመልካቹ ይሰጣል።

፪. ፕሮጀክቱ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያስከትል ሆኖ ሲያገኘው በፕሮጀክቱ ላይ በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች መሠረት የጥናት ትኩረት በመወሰን የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት እንዲካሄድበት ያደርጋል።

፲. <u>የጥናት ትኩረት ስለመወሰን</u>

፩. በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እና ይህን ደንብ ለማስፈጸም የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የፕሮጀክቱ ባለቤት የጥናቱን ትኩረት አዘጋጅቶ ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት።

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሠረት የሚዘጋጀው የጥናት ትኩረት፦

ሀ. የፕሮጀክቱን ባህሪ፣ መጠንና ሥፍራ፣

ለ. የስፍራውን ነባርና የወደፊት የአጠቃቀም ዕቅድ፣

ሐ. በማህበራዊ እና በተፈጥሮአዊ አካባቢ ላይ የሚከተለውን አሉታዊ ተጽዕኖ፣

መ. የተፈጥሮ ሀብት አቅርቦት ግምት፣

ሠ. በፈሳሽ፣ በጠጣር፣ በብናኝ፣ በጋዝ እና በድምፅ መልክ ተፈጥረው ወደ አካባቢ የሚለቀቁ የበካዮች ግምታዊ መጠንና ዓይነት፣

ረ. በመሬት፣ በአየር ወይም በውሀ ላይ የሚከተለውን አሉታዊ ተፅዕኖ፣

ሰ. በፕሮጀክቱ አካባቢ ያሉና በቀላሉ የሚጎዱ ወይም ይጎዳሉ ተብለው የሚታሰቡ ክፍለ አካባቢዎች፣

ሸ. ፕሮጀክቱ አግባብ ካላቸው ፖሊሲዎች እና ሕጎች ጋር ያለውን መጣጣም፣

ቀ. ከአስተዳደሩ ውጭ ሊከተል ስለሚችል አሉታዊ ተፅዕኖ፣

በ. የተፅዕኖ መቋቋሚያ እርምጃዎች፣ አማራጭ የመፍትሔ ሃሳቦች እና ሌሎች በባለሥልጣኑ የሚገለጹ ተፈላጊ ሁኔታዎችን ማካተት ይኖርበታል።

፲፩. <u>የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ሰነድ መያዝ ያለበት ጉዳዮች</u>

፩. የተፅዕኖ የጥናት ሰነድ በቀላል ቋንቋና አገላለጽ የጥናቱን አጭር መግለጫ የያዘ መሆን አለበት። ሆኖም ዝርዝር ቴክኒካዊ ትንታኔዎች እና መረጃዎች በአባሪነት ማያያዝ ወይም በግርጌ ማስታወሻ ማመልከት ይቻላል።

፪. የተፅዕኖ የጥናት ሰነድ ለጥናቱ ዝግጅት የዋለ መረጃን፣ በጥናቱ ወቅት ያጋጠመ አጠራጣሪ ሁኔታን ወይም የዕውቀት ክፍተትን ማመልከት አለበት።

2. The Authority shall undertake refining assessment on applicant project by receiving the project describing document and application in accordance with sub-Article (1) of this article.

3. The Authority may use any information for the undertaking of censorship on the project. However, when it found the submitted information are not sufficient to give decision, the authority shall cause to undertake the necessary study and to be submitted fully thereof.

*9. Decision of refinement*

After finalizing the task of censorship and refinement, the Authority shall:

1. Where it is found that the project is not likely to entail significant impact, issue evidence to the applicant indicating the agreement to implement the project.
2. Where it is found that the project is likely to entire significant impact, by determining study focus in accordance with the provisions of these regulations, cause to undertake environmental impact assessment on the project.

*10. Determining Study Focus*

1. By following the provisions of these regulations and a directive issued for the implementation of same, the proponent by preparing study attention shall submitte to the Authority.
2. A study focus prepared in accordance with sub-Article (1) of this article shall include:

(a) Characteristics of the project, size and area;

(b) The existing and the future utilization plan of the area;

(c) A negative impact on social and natural environment;

(d) The estimate of natural resources supply;

(e) The estimated pollutant created in the form of liquid, solid, dust, gas and voice amount or kind released to the environment

(f) A negative significant impact on land, air or water;

(g) Sub- environments found in the project area and are easily affected or likely to be affected;

(h) Conformity of the project with appropriate policies and laws;

(i) A negative impact be followed outside the government land;

(j) Measures to resist impact, alternative solution ideas and other necessary conditions specified by the Authority.

*11. Matters constituted in the environmental impact study Instrument*

1. The impact study instrument shall include in a simple language and elaboration and a brief summarizing statement of the study. However, it may indicate detail technical analysis and attach information in the annex or on the footnote.
2. The study instrument shall include the information used for the preparation of the study, doubtful condition that occurred during the study period or the gap of knowledge.

፲፪ <u>የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ሰነድ ቀዳሚ ምርመራ</u>

፩. ባለሥልጣኑ የቀረበለትን የተፅዕኖ የጥናት ሰነድ መንግሥታዊ መ/ቤቶች፣ የአካባቢው ህብረተሰብ አግባብነት እና ፍላጎት ያላቸው ሁሉ በ15 ቀናት ውስጥ አስተያየት እንዲሰጡበት ያደርጋል::

፪. ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ(1) መሰረት የተሰጠውን አስተያየት እና የቀረበለትን የጥናት ሰነድ በዚህ ደንብ ድንጋጌዎች እና በፀደቀው ጥናት ትኩረት ላይ በመመሥረት ይመረምራል::

፫. የጥናቱ ሰነድ የዚህን ደንብ ድንጋጌዎችና በሌሎች መመሪያዎች የተመለከቱ ተፈላጊ ሁኔታዎችን የፕሮጀክቱ ባለቤቱ እንዲያሟሉ ካደረገ ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ አንቀፅ 13 መሠረት ይፈጽማል:: ሰነዱ ይህንን ካላሟላ ግን የፕሮጀክቱ ባለቤት አስፈላጊውን ማስተካከያ እንዲፈጽም ባለስልጣኑ ያደርጋል፡፡

፬. ባለስልጣኑ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (3) መሠረት ተስተካክሎ የቀረበው የጥናት ሰነድ በደረሰው በአሥር ቀናት ውስጥ ሰነዱ ተስተካክሎ ስለመቅረቡ ወይም ስላለመቅረቡ ወሳኔ መስጠት አለበት::

፲፫. <u>የክትትል መርሀ ግብር ዝግጅት</u>

፩. ባለሥልጣኑ በጥናት ሰነዱ ላይ ምርመራ ካካሄደ በኋላ ፕሮጀክቱ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ እንደሚያደርስ ሲያረጋግጥ የክትትል መረሀ ግብር ያዘጋጃል::

፪. ባለስልጣኑ ፕሮጀክቱ የሚያስከትለውን ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ መቋቋም የማይቻል ሆኖ ሲያገኘውና ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዳይሆን ሲወሰን ይህንኑ ውሳኔ ለፕሮጀክቱ ባለቤት ከነምክንያቱ በፅሁፍ ያስታውቃል::

<u>ክፍል ሶስት</u>

<u>የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት፣ ዘገባ እና ምርመራን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች</u>

፲፬. <u>የፕሮጀክት ባለቤት ግዴታዎች</u>

፩. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት የፕሮጀክቱን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አካሄዶ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን በቅድሚያ ለይቶና ተፅዕኖዎቹን የማስቀሪያ ወይም የመቋቋሚያ ዘዴን በጥናቱ ውስጥ አካትቶ ባለሥልጣኑ ተገቢነታቸውን ከወሰነላቸው ሰነዶች ጋር የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባን ለባለሥልጣኑ ማቅረብ አለበት::

፪. በፕሮጀክቱ ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚካሄደው እና የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባም የሚዘጋጀው ባለሥልጣኑ በሚያወጣው መመሪያ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን በሚያሟሉ ባለሙያዎች መሆኑን የፕሮጀክቱ ባለቤት ማረጋገጥ አለበት::

፫. የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን ለማካሄድና የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባን ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን ወጪ የፕሮጀክቱ ባለቤት መሸፈን አለበት::

፬. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት ፕሮጀክቱን ሲተገብር በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ማሟላት አለበት::

12. *Censorship of Environmental impact study Document*

1. The Authority shall cause government offices, local communities, appropriate and interested groups within 15 days to give opinion on the submitted impact study document.
2. The Authority shall examine the given opinion and the submitted study document by virtue of sub-Article (1) of this article based on the provisions of these regulations and on approved study focus.
3. The Authority shall implement in accordance with Article(13) of these regulations when the study document fulfilled the provisions of these regulations and the necessary conditions specified under other directives by the proponent. The Authority shall cause the proponent to make the necessary modification while the document has failed to fulfill therein.
4. The Authority shall give its decision within ten days upon receipt of modified study document weather the document has been modified or not in accordance with sub-Article (3) of this Article.

13. *preparation of action plan for Monitoring*

1. The Authority after having undertaken review on study instrument and where the project is believed to have adverse negative impact, it shall prepare monitoring action plan.
2. Where the Authority has found that the significant negative impact of the project is irresistible and has given the decision not to implement such project, it shall notify same in a written form to the proponent with the reasons thereof.

*PART THREE*

*Environmental Impact study, Report and Provisions Concerning review of Report*

14. *Duties of a proponent*

1. A Proponent Shall undertake an environmental impact assessment, identify the likely adverse impacts of his project, incorporate the means of their prevention or containment, and submit to the Authority the environmental impact study report together with the documents determined as necessary by the Authority.
2. A proponent shall ensure that the environmental impact assessment of his project is conducted and the environmental impact study report is prepared by experts that meet the requirements specified under a directive issued by the Authority.
3. The cost of undertaking an environmental impact assessment and preparing an environmental impact study report shall be born by the proponent.
4. When implementing his project, a proponent shall fulfill the terms and conditions of his authorization.

፲፭. <u>የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ይዘት</u>

፩. የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ባለሥልጣኑ የፕሮጀክቱን መካሄድ ወይም አለመካሄድ ተገቢነት እንዲሁም ሲካሄድ ሊኖረው የሚገባውን ሁኔታ ለመወሰን የሚያስችለው በቂ መረጃ የያዘ መሆን አለበት::

፪. የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን አለበት::

ሀ. የፕሮጀክቱን ባህሪ፣ በጥቅም ላይ የሚውለውን ቴክኖሎጂና አጠቃቀም፣

ለ. ፕሮጀክቱ ሲተገበር እንዲሁም ቋሚ ሥራው ሲከናወን ወደ አካባቢ የሚለቀቀውን የበካይ ይዘትና መጠን፣

ሐ. የሥራው እንቅስቃሴ የሚጠይቀው የኃይል ፍጆታና ምንጭ፣

መ. ከአስተዳደሩ ውጭ ሊከተል ስለሚችል የአካባቢ ተፅዕኖ መረጃ፣

ሠ. በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይከተላሉ ተብለው የተገመቱ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ባህርያትና የሚቆዩበት ጊዜ፣

ረ. አሉታዊ ተፅዕኖን ለማስወገድ፣ ለመቀነስ ወይም ለማቃለል የታቀዱ እርምጃዎች፣

ሰ. የአካባቢ አያያዝ ችግርን ለማቃለል የተነደፉ ዕቅዶች፣ የአደጋ መከላከያ ዝግጁነት፣ እና

ሸ. ፕሮጀክቱ በሚተገበርበትና ቋሚ ሥራው በሚከናወንበት ወቅት የውስጥ ቁጥጥርና የክትትል ሥራዎች የሚካሄዱባቸው መንገዶች፣

፫. ባለሥልጣኑ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባን ለማዘጋጀትና ዘገባውን ለመመርመር የሚረዱ ሃሳቦችን የሚዘረዝሩ መመሪያ ዎችን ማውጣት አለበት::

፲፮. <u>የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ምርመራ</u>

፩. ምርመራ እንዲካሄድበት ለባለሥልጣኑ የሚቀርብ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ለማንም ሊረዳ በሚችል ቋንቋ በአጭሩ የተዘጋጀ፣ የጥናቱን ማብራሪያ የያዘና እንዲሁም የጥናቱ መረጃ መሟላቱንና ትክክለኛነቱን የሚያመለክት አጭር መግለጫ የያዘ መሆን አለበት::

፪. ባለሥልጣኑ በ15 የሥራ ቀናት ውስጥ የህዝብ አስተያየትና የባለሙያዎችን ሀሳብ በማመዛዘን የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናቱን ዘገባ ከመረመረ በኋላ:-

ሀ. ጎጂ ተፅዕኖ የማያስከትል መሆኑን ካመነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፕሮጀክቱን ይቀበላል:: እንዲተገበርም ይሁንታውን ይሰጣል::

ለ. ጎጂ ተፅዕኖዎቹን ለማስቀረት ወይም በበቂ ሁኔታ ለመቋቋም የሚቻል መሆኑን ካመነ ለማስቀረት ወይም ወደ ኢምንትነት ለመቀነስ የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች ዘርዝሮ እንዲሟሉ በማዘዝ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ ይሰጣል:: ወይም:-

ሐ. ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በአካባቢ ላይ የሚከተለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በአጥጋቢ ሁኔታ ለማስቀረት እንደማ ይቻል ካመነ የፕሮጀክቱን ትግበራ ይከለክላል::

*15. Content of Environmental Impact Study Report*

1. An environmental impact study report shall contain sufficient information to enable the Authority to determine weather and under what conditions the project shall proceed.
2. An environmental impact study report shall contain, as a minimum, a description of:
   a) The nature of the project, including the technology to be used and mode of operation to be followed;
   (b) The content and amount of pollutant that will be released during implementation as well as operation;
   (c) Source and amount of energy required for operation;
   (d) Information on the impact outside the government boarder;
   (e) Characteristics and duration of all the estimated direct or indirect, positive or negative impacts.
   (f) Measures proposed to eliminate, minimize, or mitigate negative impacts;
   (g) Contingency plan incase of accident; and
   (h) Procedures of self-auditing and monitoring during implementation and operation.
3. The Authority shall issue guidelines that determine the elements necessary to prepare as well as evaluate an environmental impact study report.

*16. Review of Environmental Impact Study Report*

1. An environmental impact study report that is submitted to the Authority for review shall include a brief statement summarizing the study in non-technical terms as well as indicating the completeness and accuracy of the information given in the study report.
2. The Authority shall, after evaluating an environmental impact study report by taking in to account any public comments and expert opinions, within 15 working days:
   (a) Approve the project without conditions and issue authorization if it has convinced that the project will not cause negative impacts.
   (b) Approve the project and issue authorization with conditions that must be fulfilled in order to eliminate or reduce adverse impacts in to insignificance if it has convinced that the negative impacts can be effectively countered; or
   (c) Refuse implementation of the project if it has convinced that the negative impact can not be satisfactorily avoided.

፲፯. <u>የአካባቢ ተፅዕኖ የመገምገም ሥልጣን</u>
ፈቃድ የመስጠቱ፣ የመተግበሩ ወይም የአተገባበር ቁጥጥር ድርሻ የአስተዳደሩ ከሆነና ፕሮጀክቱ በአስተዳደሩ ጎረቤት ክልል ላይ ተፅዕኖ ያስከትል ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ከሆነ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባውን የመመርመር፣ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ የመስጠትና አተገባበሩን የመከታተል ኃላፊነት የባለሥልጣኑ ይሆናል፡፡

፲፰. <u>መረጃ የመሰብሰብ ሥልጣን፦</u>
ባለሥልጣኑ በዚህ ደንብ መሠረት ተግባሩን ለመወጣት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎችን ከማንኛውም ሰው የማግኘት ወይም ላዘዘለት እንዲሰጥለት የማድረግ ሥልጣን አለው፡፡

፲፱. <u>የፀደቀ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ የውሳኔ አሰጣጥ</u>
፩. እንዲተገበር ይሁንታ የተሰጠው የአንድ ፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ይኸው ይሁንታ ሲሰጥ አብሮ የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ተከትሎ ካልተተገበረ ተፈፃሚነቱ ይቀራል፡፡
፪. የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ በሱ ላይ ተፈፃሚ መሆኑ ተገቢ አለመሆኑን ሊያስረዳ የሚፈልግ የፕሮጀክት ባለቤት ለባለሥልጣኑ ማመልከት ይችላል፡፡
፫. ልዩ ሁኔታ ካላስገደደው በስተቀር ባለሥልጣኑ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት ማመልከቻውን ከተቀበለበት ዕለት ጀምሮ በሰላሳ ቀናት ውስጥ የዘገባው ተቀባይነት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዲራዘም ወይም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ መወሰን አለበት፡፡

## ክፍል አራት
## የመንግስት ሰነድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ

፳. <u>የመንግስት ሰነድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ</u>
፩. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት በወጣ መመሪያ በሚገለፅ መደብ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም የመንግሥት ሰነድ ከመፅደቁ በፊት ስልታዊ የተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድበት መደረግ አለበት፡፡
፪. በባሕሪያቸው ቸል ሊባሉ የማይችሉ አካባቢዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው የሚገመቱ የመንግስት ሰነዶችን መደብን ለመለየትና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድባቸው ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ባለሥልጣኑ ማውጣት አለበት፡፡
፫. በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ(2) በወጣ መመሪያ መሠረት ስልታዊ የተፅዕኖ ግምገማ በሚያስፈልገው መደብ የሚካተትን ማናቸውም የመንግሥት ሰነድ የሚያዘጋጅ የመንግሥት አካል በሰነዱ ላይ ስልታዊ የተፅዕኖ ግምገማ የተካሄደበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡
፬. ማናቸውም የመንግሥት አካል የሚያዘጋጀው ማናቸውም የመንግሥት ሰነድ ሊያስከትለው የሚችለው ተፅዕኖ እንዲገመገም ለማስቻል ከባለሥልጣኑ ጋር መተባበር አለበት፡፡

## ክፍል አምስት
## ከተፅዕኖ ግምገማ በኋላ ስለአሉ ሁኔታዎች

፳፩. <u>የአዲስ ሁኔታ መከሰት</u>
የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ከቀረበ በኋላ ከባድ እንድምታ ያለው ቀደም ሲል ያልተጤነ ዕውነታ ቢከሰት ባለሥልጣኑ እንድምታውን ለማጤን እንዲችል የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው እንደአስፈላጊነቱ እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ ማዘዝ ይችላል፡፡

*17. Power to Evaluate Environmental Impact*
The Authority shall be responsible for the evaluation and authorization of any environmental impact study report and the monitoring of its implementation if the project is subjected to licensing execution and supervision by the Government and if it is unlikely to produce negative impact on neighboring regions.

*18. Power to collect information*
In order to attain its function in accordance with these regulations, the authority shall have the power to acquire the necessary information from any person or cause to give to order.

*19. Deciding Validity of approved environmental impact study Report*
1. The authorization of an environmental impact study report shall expire if the project has not been implemented according to the time frame set during its authorization.
2. A proponent who wishes to challenge the appropriateness of the provision of sub-Article (1) of this Article to his project, may submit an application to that effect to the Authority.
3. Within 30 days from the receipt of an application pursuant to sub- Article (2) of this Article, the Authority shall, unless special circumstance dictates, decide weather to extend the validity of the report or to order the revision or the reproducing of the environmental impact assessment.

## *PART FOUR*
## *Environmental Impact Assessment of Public Instrument*

*20. Environmental Impact Assessment of public Instrument*
1. A Public instrument included in any category in a directive issued pursuant to Sub- Article (2) herein, shall, prior to approval, be subject to strategic environmental impact assessment.
2. The authority shall issue directive to determine the category as of public instruments which are likely to entail significant environmental impact and the Procedure of their impact assessment.
3. Any organ /body which initiates a public instrument falling into any category which requires environmental impact assessment as determined in a directive issued pursuant to sub- article (2) of this article shall ensure that it has been subjected to strategic environmental impact assessment.
4. Any government organ shall collaborate with the Authority to enable the evaluation of likely environmental impacts of any public instrument prepared by it.

## *PART FIVE*
## *Conditions to exist after Impact Assessment*

*21. Occurrence of New Circumstance*
If an unforeseen fact of serious implication is realized after the submission of an environmental impact study report, the Authority, as may be appropriate, may order the environmental impact assessment to be revised or redone in order to address the implication.

፳፪. <u>የትግበራ ክትትል</u>

፩. የፕሮጀክቱ ባለቤት ፕሮጀክቱ በመተግበር ላይ የሚገኘው ለፕሮጀክቱ ትግበራ ይሁንታ በተሰጠበት ወቀት በገባው ቃልና በተጣለበት ግዴታ መሠረት መሆኑ ለመገምገም ባለሥልጣኑ በፕሮጀክቱ አተገባበር ላይ ክትትል ያደርጋል፡፡

፪. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት እንዲተገብረው ይሁንታ የተሰጠውን ፕሮጀክት በገባው ቃል ወይም በተጣለበት ግዴታ መሠረት ካልተገበረ ባለሥልጣኑ መውሰድ ያለበትን የዕርምት እርምጃ በመግለፅ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል፡፡

፫. ባለሥልጣኑ ማናቸውም ፕሮጀክት እንዲተገበር በዚህ ደንብ አንቀፅ 16(2) (ሀ) ወይም (ለ) መሠረት የሰጠውን ይሁንታ ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ሌላ ፈቃድ ሰጭ መሥሪያ ቤት ለፕሮጀክቱ ትግበራ የሰጠውን ፈቃድ ይህንኑ ውሳኔ ተከትሎ ማገድ ወይም መሠረዝ አለበት፡፡

## ክፍል ስድስት
## <u>የሕዝብ ተሳትፎ፣ ማበረታቻ እና ቅሬታ አቀራረብን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች</u>

፳፫. <u>ስለሕዝብ ተሳትፎ</u>

፩. ባለሥልጣኑ ማንኛውንም የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ በዘገባው ላይ የሕዝብ አስተያየት መጠየቅ አለበት፡፡

፪. ባለሥልጣኑ በአጠቃላይ የህዝብ በተለይም ደግሞ የፕሮጀክቱ አተገባበር ጉዳት ያስከትልባቸው ይሆናል ተብለው የሚገመቱ ማኅበረሰቦች አስተያየት በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናቱ ውስጥ መካተቱን እንደዚሁም ምርመራው በሚካሄድበት ወቅት መጤኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

፳፬. <u>ስለ ማበረታቻ</u>

በፌዴራል መንግሥት በሚወጣው ደንብ መሠረት አስተዳደሩ ማበረታቻ ይሰጣል፡፡

፳፭. <u>የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት</u>

፩. ለፕሮጀክቱ ትግበራ በተሰጠ ይሁንታ ወይም በክትትል ወይም ፕሮጀክቱን በሚመለከት ከባለሥልጣኑ በተሰጠ በማናቸውም ሌላ ውሳኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን ለባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /1/ በተደነገገው መሠረት የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ቅሬታው በደረሰው በሰላሣ ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት፡፡

፫. የባለሥልጣኑ ሥራ አስኪያጅ ውሣኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡ ሆኖም በተሰጠው ውሣኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ጉዳዩ ሥልጣን ባለው ፍ/ቤት እንዲታይለት ሊያቀርብ ይችላል፡፡

*22. Implementation Monitoring*

1. The Authority shall moni implementation of an authorized project in order to evaluate compliance with all commitments made by, and obligations imposed on the proponent during authorization.
2. When the proponent fails to implement the authorized project in compliance with the commitments he entered into or obligations imposed upon him, the Authority may order him to undertake specified erectification measure.
3. Any other authorizing or licensing agency shall, in tandem with the authority's decision suspend or cancel authorization to implement a project, Where the authority suspend or cancel the license it may have issued in favor of the project in accordance with article 16 sub-article 2 a or b of theses regulations.

## *PART SIX*
## *Provisions Concerning to Public Participation, Incentive and Grievance Procedure*

*23. Public Participation*

1. The Authority shall make any environmental impact study report accessible to the Public and solict comments on it.
2. The Authority shall ensure that the comments made by the public and in particular by the communities likely to be affected by the implementation of a project are incorporated in to the environmental impact study report as well as in its evaluation.

*24. Incentive*

The Government shall give incentive in accordance with the regulations to be issued by the Federal Government

*25. Grievance Procedures*

1. Any Person dissatisfied with the authorization or monitoring or any decision of the Authority regarding the project may submit a grievance notice to the General manager of the Authority.
2. The general manager of the Authority shall, as provided under sub-Article (1) of this article give his decision on the matter within 30 days following the receipt of the grievance.
3. The decision of the general manager of the Authority shall be final. However, a party who has complain against the decision, he may lodge his matters to be adjudicated to the court having jurisdiction.

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

**፳፮. ስለ ጥፋትና ቅጣት**

፩. በዚህ ደንብ ተላላፊዎች ላይ የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ-ድንጋጌዎች ተፈፃሚነታቸው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ ይህን ደንብና ደንቡን ተከትሎ የሚወጡ መመሪያዎችን ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ሰው ከዚህ በታች የተመለከተው ቅጣት ይፈፀምበታል::

፪. ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድበት የተደነገገበትን ማንኛውንም ፕሮጀክት ከባለሥልጣኑ ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም በአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባው ውስጥ ሀሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ ከሀምሣ ሺህ ብር በማያንስና ከአንድ መቶ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል::

፫. ማንኛውም ሰው በዚህ ደንብ መሠረት ፈቃድ ሲሰጠው የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ ወይም ተፈላጊ ዝርዝሮችን በመዝገብ ሳያሰፍር ከቀረ ከአሥር ሺህ ብር በማያንስና ከሃያ ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል::

፬. በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ጥፋት ሲፈጽም የሕጉን መከበር ለማረጋገጥ መፈፀም የሚገባውን ተግባር በትጋት ያልተወጣ በመሆኑ የድርጅቱ የሥራ መሪ በንዑስ አንቀፅ ሁለት እና ሶስት ከዚህ በላይ ድርጅቱ ላይ ከተጣለው ቅጣት በተጨማሪ ከአምስት ሺህ ብር በማያንስና ከአሥር ሺህ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጫ ይቀጣል::

፭. ይህን ደንብ ወይም በሥሩ የሚወጣውን ማንኛውም መመሪያ በመጣስ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበት ሰው ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ የደረሰውን እና ወደፊትም ሊደርስ የሚችለውን ጉዳት በሙሉ በራሱ ወጪ እንዲያስተካክል ወይም እንዲተካ ፍ/ቤቱ ያዛል::

**፳፯. የመተባበር ግዴታ**

ለዚህ ደንብ አተገባበር ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት::

**፳፰. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጐች**

ከዚህ ደንብ ጋር ተቃራኒ የሆኑ ሕጐች ወይም አሰራሮች በዚህ ደንብ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖራቸውም::

**፳፱. ደንቡ የሚፀናበት ጊዜ**

ይህ ደንብ በነጋሪ ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፳፮/፲፱፻፺፰ ዓ.ም.
የአዲስ አበባ ከተማ ጊዜያዊ
አስተዳደር

## *PART SEVEN*
## *Miscellaneous Provisions*

*26. Offences and penalties*

1. Without prejudice to the implementation of the provisions of the penal code on those who violate these regulations, any person who violates these regulations and subsequent directives to be issued, the following penalty shall be executed.

2. Any person who, without obtaining authorization from the Authority or makes false presentations in an environmental impact assessment study report shall be liable to a fine not less than fifty thousand birr and not more than one hundred thousand birr.

3. Any person if he fails to keep records or to fulfill conditions of authorization issued pursuant to these regulations, shall be liable to a fine of not less than ten thousand birr and not more than twenty thousand birr.

4. When a juridical person commits an offence, in addition to the penalty imposed in sub-Article (2) and (3) of this article, it may be meted with, the manager who failed to exercise all due diligence shall be liable to a fine. Not less than five thousand birr and not more than ten thousand birr.

5. The court may in addition to any penalty imposed on a person who has been prosecuted for an offence under these regulations or directives emanating from it, order the convicted person to restore in any other way and compensate for the damage inflicted.

*27. Duty to cooperate*

Any person shall have the duty to cooperate in the implementation of these regulations.

*28. In applicable laws*

Any law or practice in consistent with these regulations shall not be applicable on matters provided in these regulations.

*29. Effective Date*

These Regulations shall come into force on the date of its publications in the Addis Negari Gazeta.

Done at Addis Ababa
This 4th day of May 2006.

Provisional Government of Addis Ababa City